ጃንዋሪ 16, 2026

ውድ የRainier Beach ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማህበረሰብ፣

ስለ አዲሱ የ Rainier Beach ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የደህንነት ስጋት በቅርቡ በ KUOW የዜና ዘገባ መነሳቱን እናውቃለን።

ዘገባው አስደንጋጭ ቢመስልም፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤቱን ሲነድፍ እና ሲገነባ መደበኛ የደህንነት መመሪያዎችን እንደሚከተል ልናረጋግጥልዎ እንፈልጋለን።

ዘገባው ትክክል ነው፣ትምህርት ቤቱ ከመክፈቱ በፊት methane መመርመር የሚል ምክር ሃሳብ ቀርቦ ነበር። ምርመራው አልተካሄደም፣ለዚህም ይቅርታ እንጠይቃለን።

ሕንፃው ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እርግጠኞች ነን።በቅርቡ በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በተደረገው ምርመራ መሰረት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምንም አይነት methane አለመኖሩን አሳይቷል።የmethane ምርመራውን እንቀጥላለን።የበለጠ እርግጠኛ ለመሆን ምርመራ እንዲያከናውን ውጭ ኩባንያ ለመቅጠር እየሰራን ነው።ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የምርመራዎን ውጤቶችን ለማህበረሰቡ ለማጋራት ቁርጠኛ ናቸው።

በየህንፃው ግንባታ ወቅት ሁሉም የሚመከሩ የደህንነት እርምጃዎች ተካተዋል።እነዚያን የደህንነት እርምጃዎች እና እንዴት እንደተተገበሩ ከዚህ በታች እናብራራለን።

ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት፣የፕሮጀክቱን ቡድን ለማግኘት እባክዎን Let’s Talkን ይጠቀሙ።

ከሰላምታ ጋር፣

Dr. Kurt Buttleman

Assistant Superintendent of Finance

Chief Operations Officer

---

## ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች አዲስ ትምህርት ቤት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዴት እንደሚሰራ

### በዕቅድ ዝግጅት ወቅት

- ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤቱን ቦታ እንዲያጠኑ Maul Foster & Alongi (MFA) የተባለውን የታወቀ የአካባቢ ምህንድስና ድርጅት ቀጥረዋል።
    - MFA በአንዳንድ አካባቢዎች peat soil አግኝቷል።

- peat methan ማምረት ስለሚችል ተጨማሪ ምርመራዎች ተደርገዋል።
    - የ methan መጠን ከአንድ የምርመራ በታ በስተቀር በሁሉም እርምጃ ለመውሰድ ከሚያስፈልገው ደረጃ በታች ነበር።በአንድ የምርመራ  በታ እርምጃ  ለመውሰድ ከሚያስፈልገው ደረጃ ትንሽ ከፍ ያለ ነበር።
- MFA የ methane ን አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ መንገዶችን በተመለከተ ለሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ምክሮችን ሰጥቷል።
- እነዚህ ምክሮች የክልል እና የፌዴራል የደህንነት መመሪያዎችን ይከተላሉ።
    - ከህንፃው ስር methanን ማውጣት የሚችን ስርዓት መትከል።
    - ከህንፃው በታች ወፍራም የውሃ መከላከያ መትከል።
    - ከተገነባ በኋላ methaneን በቋሚነት መፈተሽ።

**ዲዛይን እና ግንባታ**

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤቱን ሲገነባ ሁሉንም የ MFA ምክረ ሃሳቦችን አካቷል።

1. **የ Methane አየር ማናፈሻ ስርዓት(Methane Venting System)**
    - በየህንፃው የኮንክሪት መሠረት ስር የአየር ማናፈሻ ስርዓት ተተክሏል።
    - ስርዓቱ ማንኛውንም methane ከጣሪያው በላይ ወደ ውጭ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲንቀሳቀስ ያደርገዋል።
    - ይህ methane ወደ ሕንፃው እንዳይገባ ይከላከላል።
2. **የውሃ መከላከያ(Waterproof Barrier)**
    - ከመሠረቱ በታች ወፍራም የውሃ መከላከያ ሽፋን ተደርጓል።
    - ይህ ሽፋን እርጥበት እና methane ወደ ሕንፃው እንዳይገቡ ያግዳል።

በግንባታው ወቅት የጥራት ፍተሻዎች ተደርገዋል።

- MFA የአየር ማናፈሻ ስርዓቱን ዲዛይን እና መትከል ገምግሟል።
- Building Envelope Technology & Research (BET&R) የተባለ የህንፃ ኤንቨሎፕ አማካሪ ድርጅት የውሃ መከላከያውን ሙሉ በሙሉ መዘጋቱን ለማረጋገጥ ክትትል አድርጓል።

**ክትትል እና ምርመራ**

MFA ሰዎች ወደ ሕንፃው ከመግባታቸው በፊት የ methane ምርመራ እንዲያደርጉ ምክረ ሐሳብ አቅርቦ ነበር ።ደረጃ በደረጃ በመክፈቱ ምክንያት ይህ እርምጃ አልተፈጸመም።አሁን ግን ምርመራው ተጀምሯል።

- በታህሳስ 9, 2025 በተደረገው ምርመራ መሰረት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምንም አይነት methane አልተገኘም።
- የመመርያ መሳሪያው methaneን ጨምሮ ሁሉንም ተቀጣጣይ ጋዞች ይፈትሻል።

ለማህበረሰቡ ተጨማሪ በራስ መተማመን ለመፍጠር፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች በሚቀጥለው ዓመት መደበኛውን ምርመራ ለመቀጠል MFAን ይቀጥራል።ከዚያ በኋላ፣ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በ MFA ግኝቶችን ላይ በመመስረት የረጅም ጊዜ የምርምርራ ዕቅድ ያወጣል።